ወርኃዊ ጥንቅር፣ ቁ.008
መስከረም 2018 ዓ.ም.



# የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ክራሞት

እንደራሴ

እንደራሴ በብሪጅ ሪሰርች እና ኢኖቬሽን በየወሩ እየተዘጋጀ ይቀርባል።

research@bridge-et.org

## መልክዓ-ብሪጅ

መቀመጫውን አዲስ አበባ ያደረገ፣ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ዐዋጅ ቁጥር 1113/2011 መሰረት አገር በቀል የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት ሆኖ የተመዘገበ የጥናትና ምርምር ተቋም ነው። ብሪጅ፣ በዋናነት በኢትዮጵያ እና በምሥራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግሥታት (ኢጋድ) አባል አገራት ውስጥ ዲሞክራሲያዊ አሠተዳደር እንዲጎለብት እና ሰላም እንዲበለጽግ የሚሠራ ገለልተኛ እና ለትርፍ ያልተቋቋመ ፖሊሲ ተኮር የጥናት እና ምርምር ተቋም ነው።

## ተልዕኮ

ዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እና ሰላም ይጎለብት ዘንድ፣ ለፖሊሲ አወጣጥ ግብዓት የሚሆኑ፣ ተጨባጭነት ያላቸው ምርምሮችን ማድረግ እና የፖሊሲ ምክረ ሐሳቦችን ማቅረብ፤

## ርዕይ

በሕዝብ ተወካይ ምክር ቤቶች እና በቀጠናዊ የሰላም፣ ዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እና ሰዋዊ እና ቁሳዊ ልማት ላይ፣ በኢጋድ ቀጠና ተቀዳሚ የምርምር እና ፖሊሲ አመንጪ ማዕከል መሆን፤

## መሠረታዊ ዕሴቶች

- አጽንዖተ ትኩረት፦ ከፍተኛ ትኩረት የተሰሩ እና ተጨባጭነት ያላቸው ጥናት ምርምሮችን ማቅረብ።።
- አዲስነት፦ ለዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እና ሰላም ተግዳሮቶች ፈጠራዊ እና ተለዋዋጭ መፍትሔዎች የታከለባቸውን የመፍትሔ ሐሳቦች ማዋጣት
- ታማኝነት፦ ተዓማኒነት ያላቸውን የምርምር ውጤቶችን በማቅረብ ተዓማኒነትን መጠበቅ

## ግቦች

ኢትዮጵያ እና በኢጋድ ቀጠና የሚገኙ የፌዴራል እና የክልል ፓርላማዎች በሚከተሉት መንገዶች ማጠናከር

- ተጨባጭ ምርምሮችን መከወን
- የእንደራሴዎችን ብቃት ለማሳደግ የዐቅም ግንባታ ድጋፎችን ማድረግ
- ተጠያቂነትን እና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ የሕዝብ ተወካይ ምክር ቤቶች ክንውኖችን መከታተል

**BRIDGE** Research & Innovation-
Parliaments. Peace. Policy

+251 911 86 12 34

+251 115 57 74 96

research@bridge-et.org

https://bridge-et.org/

150096, Addis Ababa, Ethiopia.

Kazanchis, across the main gate of UNECA, SA Building, 9th Floor, Office No. 5, Addis Ababa.









# ማውጫ


በወሩ የተካሄደ የምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ ........ 1

ፕሬዝደንቱ ይናገራሉ ........ 2

የአሥፈጻሚ ተቋማት ቁጥጥር ........ 5

የእንደራሴዎቹ የውክልና ሥራ ........ 7

የፓርላማ ዲፕሎማሲ ........ 11

እንደራሴዎቹ ስለ'ራሳቸው በ'ራሳቸው ........ 13

የብሪጅ ዕይታ በስምምነቱ ሰነድ ዙሪያ ........ 15

የኢትዮጵያ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ ከሐምሌ 1 እስከ መስከረም 26 ቀን 2018 ዓ.ም. ባሉት ጊዜያት እረፍት ላይ ቢሰነብትም፣ የዓመቱ የመጀመሪያ ወር ያሳለፈው በዋናነት የውክልና ሥራ በመሥራት ነበር፡፡ በዚኹ መስከረም ወር አበይት የፓርላማ ክንውን የነበረው፣ ፕሬዝዳንት ክቡር ታዬ አጽቀሥላሴ በ6ኛው የሕዝብ ተወካዮች እና የፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን የጋራ የመክፈቻ ሥነ-ሥርዓት ላይ፣ የ2018 የመንግሥት ዋና ዋና የዕቅድ አቅጣጫዎችን በማቅረብ ያደረጉት ንግግር ነበር። በዚኹ ዕለት ለምክር ቤቱ አዲስ እና በጎ የአሰራር ጅማሮ የሆነው የኢቲቪ-ፓርላማ የቴሌቪዥን ቻናል መከፈቱም የተነገረበት ነበር፡፡ በተጨማሪም ለተቋማችን ብሪጅ ሪሰርች ኤንድ ኢኖቬሽን ግዙፍ የሥራ ምዕራፍን የሚከፍተው፣ ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት ጋር የተደረገው የጋራ ሥምምነትም አንዱ አንኳር የወሩ ግብር ነበር። ይኽች የብሪጅ ስምንተኛ እና የዓመቱ የመጀመሪያ ዕትምም፣ የምክር ቤቱን የመስከረም ክራሞት እና ተቋማችን ከምክር ቤቱ ጋር ያደረገውን የስምምነት ነጥቦች አጠናክራ ቀርባለች።

# በወሩ የተካሄደ የምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ

6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን

መስከረም 26

የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን መክፈቻ ሥነ- ሥርዓት ጉባኤ

**አጀንዳ**

የኢፌዴሪ ፕሬዝዳንት ክቡር ታዬ አፅቀ ሥላሴ ለኹለቱ የፌደራል መንግሥት ምክር ቤቶች ዓመታዊ ሥራቸውን መጀመራቸውን በማብሰር የፌዴራል መንግሥቱን ዓመታዊ ዕቅድ መስማት

መስከረም 26

1ኛ መደበኛ ስብሰባ

**Agenda**

የኢፌዴሪ ፕሬዝደንት ክቡር ታዬ አፅቀስላሴ መስከረም 26 ቀን ፣ 2018 ዓ.ም. ለሕዝብ ተወካዮች እና ለፌዴሬሽን ምክር ቤቶች የጋራ መደበኛ ስብሰባ ያደረጉትን የመክፈቻ ንግግር አስመልክቶ የቀረበን የድጋፍ ሞሽን ማዳመጥ

# ኘሬዝደንቱ ይናገራሉ

በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀፅ 58 ንዑስ አንቀፅ (2) እና በምክር ቤቱ የአሠራር እና የአባላት የሥነ-ምግባር ደንብ ቁጥር 6/2008 አንቀፅ 24 ንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት፣ የኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የአንድ ዓመት የሥራ ጊዜ ከመስከረም ወር የመጨረሻ ሳምንት ሰኞ እስከ ሰኔ 30 ቀን ድረስ መሆኑ ተደንግጓል፡፡ እንዲሁም በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 71 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ፣ የሪፐብሊኩ ኘሬዝደንት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና የፌዴሬሽኑን ምክር ቤት ዓመታዊ የጋራ ስብሰባ እንደሚከፍት ተገልጿል፡፡ በዚኽም መሰረት የ5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን የመክፈቻ ሥነ-ሥርዓት የኢፌዲሪ ኘሬዝደንት ክቡር ታዬ አፅቀ ሥላሴ፣ ኹለቱ የፌደራል መንግሥት ምክር ቤቶች ዓመታዊ ሥራቸውን መጀመራቸውን በማብሰር፣ የፌደራል መንግሥቱን ዓመታዊ ዕቅድ ሰኞ መስከረም 26 2018 ዓ.ም. አቅርበዋል፡፡ ኘሬዝደንት ታዬ በመክፈቻ ንግግራቸው ከጠቀሷቸው ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹን እንደራሴ እንደሚከተለው አጠናክራቸዋለች።



የኢፌዲሪ ኘሬዝደንት ክቡር ታዬ አፅቀ ሥላሴ ከኹለቱ የፌደራል መንግሥት ምክር ቤቶች አፈ ጉባኤዎች፤ የተከበሩ ታገሰ ጫፎ እና የተከበሩ አገኘሁ ተሻገር ጋር፤

## እንደ አጠቃሎ

የመክፈቻ ንግግራቸውን፣ የ2017 ዓ.ም. ዋንኛ የአገሪቷ ስኬቶች ያላቸውን በመጥቀስ የጀመሩት ፕሬዝደንት ታዬ አጽቀ ሥላሴ፣ የታላቁ ህዳሴ ግድብ መመረቅ፣ በወርኃ መስከረም መጀመሪያ ላይ የኢትዮጵያ የከርሰ ምድር ሀብት የብስራት ጅማሮ የሆነውን የተፈጥሮ ጋዝ ያወጣንበት እና የተፈጥሮ ሀብታችን በመጠቀም የእድገታችንን መልህቅ የሆኑ ግዙፍ ፕሮጀክቶችን የጀመርንበት በመሆኑ፣ ይህ ዘመን በታሪካችን ውስጥ በጉልህ የሚወሳ አዲስ ምዕራፍ ሊሆን እንደሚችል አልጠራጠርም ሲሉ ንግግራቸውን አሀዱ ብለዋል።

በ2018 ዓ.ም. በኹለቱ ምክር ቤቶች መክፈቻ ንግግራቸው ላይ፣ የአገሪቷን የፖለቲካ እና የጂኦስትራቴጂካዊ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች በስፋት ያነሱት ፕሬዝደንት ታዬ፣ ከሥርዓት መለዋወጥ ጋር የማይናዱ ነጻ፣ ገለልተኛ እና ሕዝባዊ ብሔራዊ ተቋማትን ለመፍጠር መንግሥት ጽኑ መሠረት በመጣል ላይ ይገኛል ሲሉ ተደምጠዋል። አክለውም ብሔራዊ የጸጥታ እና የደኅንነት ተቋማት የሥርዓት ለውጥን የሚሻገሩ እና ብርቱ እንዲሆኑ መንግሥት በቁርጠኝነት እንደሚተጋ ገልጸዋል። ምንም እንኳን በየጊዜው የሚስተዋሉ የኃይል እንቅስቃሴዎችን ለማስቆም መንግስት ሙሉ ዝግጁነት እና ዘመናዊ አቅም ቢኖረውም፤ ‘የዛሬውን ግጭት በማሸነፍ ለነገው ትውልድ ቂምና ቁርሾ አናወርስም’ የሚልን መርህ በመከተል በዛሬ ብልሃት እና ትግስት ለነገ ዘላቂ ሰላም የሚበጅ አካሄድን መርጧል ሲሉ የመንግሥታቸውን አቋም ለእንደራሴዎቹ ነግረዋቸዋል። ከዚኽም ጋር በተያያዘ ለአገራዊ ምክክሩ ስኬታማነት መላው ሕዝብ እና ልሂቃን የበኩላቸውን እንዲወጡ ጥሪ አቅርበዋል። ለሕዝብ የቀረበ እና ለሕግ የታመነ አሥተዳደር ወደ ብልፅግና ለሚደረገው ጉዞ ወሳኝ መሆኑን ጠቁመው፣ ይህንንም እውን ለማድረግ መንግሥት የአሥተዳደር ማዕቀፎችን በማሻሻል፣ የተቋማትን ቅንጅት በማጠናከር እንዲኹም ተመሳሳይ እና ተጓዳኝ ዘርፎችን በማሰባሰብ ውጤታማ እንዲሆኑ አድርጓል ሲሉም ተሰምተዋል።

## ኢኮኖሚ እና ልማት

በኢኮኖሚው ዘርፍ መንግሥት በ2018 በጀት ዓመት 9 በመቶ ጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት እድገትን ለማረጋገጥ እንደሚተጋ የጠቀሱት ርዕሰ-ብሔሩ፣ ለዚኽ ዕቅድ ስኬታማነትም መንግሥት ምርትን በብዛት፣ በዓይነት እና በጥራት ያሳድጋል ብለዋል። መንግሥት ባለፉት ዓመታት ጠንካራ የፊሲካል እና የገንዘብ ፖሊሲዎችን ተግባራዊ በማድረግ፣ ምርት እና ምርታማነትን በማሳደግ የዋጋ ግሽበት እንዲቀንስ ጉልህ ጥረት ለእንደራሴዎቹ ያስታወሱት ፕሬዝደንት ታዬ፣ በዚኽ ዓመት ይህ ተጠናክሮ የዋጋ ግሽበቱ ወደ ነጠላ አሃዝ እንዲወርድ ይደረጋል ሲሉ በአጽንዖት ተናግረዋል። የግብርናው የልማት ዘርፍ ኹለንተናዊ ብልፅግናን ለማረጋገጥ ወሳኝ መሆኑን መንግሥት በእጅጉ ያምናል ሲሉ የተደመጡት ፕሬዝደንቱ፣ በያዝነው ዓመትም ግብርናው ከባህላዊ የአመራረት ከፍ ብሎ በቴክኖሎጂ፣ በፋይናንስ አቅርቦት እና በክህሎት ልማት እንዲደገፍ፣ ልዩ ትኩረትን በመስጠት የ6.8 በመቶ እድገት እንዲያስመዝግብ ይደረጋል ማለታቸውን ሰምተናል። የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ ባሻገር የምግብ ሉዓላዊነታችንን የምናጸናበት ዘመንም ይሆናል ያሉት ርዕሰ-ብሔሩ፣ የግብርና ግብአቶች በአገር ውስጥ ማምረት፣ በተለይም የተጀመረውን የማዳበሪያ ፋብሪካ ግንባታ ማፋጠን፣ ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ይሆናሉም ብለዋል። ምርታማነትን የሚያሳድጉ አካሄዶችን፣ የግሉ ዘርፍ ተሳትፎን የሚጨምሩ ስትራቴጂዎችን፣ አገራዊ ቁጠባ እና የመዋዕለ-ንዋይ ፍሰትን የሚያጎለብቱ ስልቶችን ተግባራዊ ለማድረግም እንደሚሰራ ፕሬዝደንቱ ተናግረዋል። ከዚኽ ባለፈም፣ የዲጂታል ቴክኖሎጂን በማስፋት፣ የመረጃ ልውውጥን በማቀላጠፍ እና አገልግሎቶችን ተደራሽ በማድረግ፤ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግርን በአጭር ጊዜ እውን ማድረግ እንደሚቻል መንግስት በጽኑ እንደሚያምን አትተዋል።



# የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ጉዳዮች

በውጪ ጉዳይ ፖሊሲ ረገድ አራት ጉዳዮች በቀዳሚነት እንደሚከናወኑ ያነሱት ፕሬዝደንት ታዬ፤ ቀዳሚው ጉዳይ፣ ዜጋን ማዕከል ያደረገ ብሔራዊ ደህንነትን ማረጋገጥ ከመሆኑ ባሻገር፣ ብሔራዊ ደህንነት የአገራችንን ዳር ድንበር ማስከበር ብቻ ሳይሆን፣ የዜጎችን ደህንነት እና ክብርንም ማስጠበቅ እንደሚጨምር ተናግረዋል። ኢትዮጵያ በአባይ እና በቀይ ባህር መሀከል የምትገኝ አገር መሆኗን በኹለተኛነት ያነሱት ፕሬዝደንቱ፣ ዕጣ ፋንታዋ እና መጻይ እድሏም ከኹለቱ ውኃዎች ጋር በእጅጉ የተቆራኘ መሆኑን በማንሳት፣ ይኹን እንጂ ኢትዮጵያ ፍትሕን ባልተከተለ መንገድ እና ሕዝብን ባላማከለ እና ባላሳተፈ አግባብ ተገልላ መቆየቷን አንስተዋል። ከዚኽ አንፃርም መንግሥት ፍትሐዊ እና አስተማማኝ የባህር በር ለማግኘት ከቀጠናው አገራት ጋር በዲፕሎማሲያዊ እና በሰላማዊ መንገድ ይሰራል ያሉት የሪፐብሊኩ ፕሬዝደንት፣ በአባይ ወንዝም ላይ የጋራ መተባበር እና መተማመን እንዲዳብር፣ የአባይ ተፋሰስ አገራትን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ተግባራትን መንግሥት እንደሚያከናውን እና እንደሚሳተፍ በዕለቱ ላገኟቸው የኹለቱን ምክር ቤት እንደራሴዎች ነግረዋቸዋል። መንግሥት በውጭ ጉዳይ ፖሊሲው "ቅድሚያ ለጎረቤት" የሚለውን መርህ አጠናክሮ መቀጠሉን በሦስተኛነት የጠቀሱት ፕሬዝደንቱ፣ ቀጠናዊ ትስስርን የሚያጠናክሩ የመሰረት ልማት ስራዎች መከናወናቸውን አንስተው፣ በቀጣይነትም ኢኮኖሚያዊ ትብብርን የሚያጎለብቱ የመሠረት ልማት ዝርጋታ እና የንግድ ልውውጥ እንዲጠናከሩ እንደሚደረግ ተናግረዋል። መንግስት በዓለም ዓቀፍ የኃይል አሰላለፎች ውስጥ ሚዛኑን በመጠበቅ፣ ትብብር እና የጋራ ተጠቃሚነትን ለማስፈን እና ለማስፋት እንደሚተጋ በአራተኛነት ያነሱት ፕሬዝደንት ታዬ፣ ከዚኽ በተጨማሪም በዓለም መድረኮች የኢትዮጵያ ተሳትፎ እና ተደማጭነት እንዲያድግ፣ የጋራ ተጠቃሚነት እንዲጎለብት፣ በዓለም ወሳኝ ጉዳዮች ላይ አገራችን ጉልህ ሚና እንዲኖራት በትኩረት ይሰራል ብለዋል።

በዓመቱ የመጨረሻ ንግግራቸው ቀጣዩን ፌደራላዊ ምርጫ ያነሱት ርዕሰ-ብሔሩ፣ በያዝነው ዓመት በአገራችን የሚካሄደው ሰባተኛ አገራዊ ምርጫ፣ ፍትሓዊ፣ ሰላማዊ፣ ዲሞክራሲያዊ እና በኢትዮጵያውያን ዘንድ ተዓማኒ ይሆን ዘንድ መንግሥት በኃላፊነት ይሰራል ሲሉ ንግግራቸውን ደምድመዋል።

# የአሥፈጻሚ ተቋማት ቁጥጥር

የ እንደራሴዎቹ ምክር ቤት የአሥፈጻሚ ተቋማትን የሚቆጣጠርባቸው መንገዶች፣ የተቋማትን ሪፖርት መስማት እና የተቋማትን እና የመስክ ጉብኝቶችን መከወን ሲሆን፣ በዚኹ ወርም የአንድ ተቋም ሪፖርትን ከማድመጡ ባለፈ፣ አንድ የመስክ ጉብኝትንም አድርጓል፡፡

## የተቋም ሪፖርት



የኢትዮጵያ አገራዊ ምክክር ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር ኘሮፌሰር መስፍን አርአያ የተቋማቸውን ሪፖርት ሲያቀርቡ፤

የኢትዮጵያ አገራዊ ምክክር ኮሚሽነሮች፣ ከኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ ታገሠ ጫፎ እና ከሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ጋር የተወያዩ ሲሆን፣ በውይይቱም የኢትዮጵያ አገራዊ ምክክር ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር ኘሮፌሰር መስፍን አርአያ፣ ባለፉት ዓመታት በምክክር ሂደቱ የተከናወኑ አጀንዳ የማሰባሰብ እና የተሳታፊ ልየታ ተግባራት አፈፃጸም ሪፖርትን አቅርበዋል። በሪፖርታቸውም፣ ከ2016 ዓ.ም. ጀምሮ አገራዊ የምክክር ሂደት የዝግጅት ምዕራፍ ክንውኖችን፣ የአጀንዳ ማሰባሰብ እና ተሳታፊ ልየታ ተግባራትን ዳሰዋል። በዚኽም በእስካሁኑ ሂደት በ11 ክልሎች እና በኹለቱ ከተማ አስተዳደሮች ስኬታማ የአጀንዳ ማሰባሰብ እና የተሳታፊ ልየታ ተግባራት ማከናወን እንደተቻለ አስታውቀዋል ተብሏል። ከዚኽ በተጨማሪም በሰሜን አሜሪካ፣ በአውሮፓ፣ በአፍሪካ እና በመካከለኛው ምሥራቅ ከሚኖሩ የትውልደ ኢትዮጵያውያን ጋር የገጽ ለገጽ እና የበይነ-መረብ ውይይት መደረጉን ማብራታቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል። በትግራይ ክልልም በአገራዊ ምክክር የአጀንዳ ማሰባሰብ እና ተሳታፊ ልየታ ማካሄድ የሚያስችሉ ቅድመ ውይይቶች መካሄዳቸውን ጨምረው ማንሳታቸው ተዘግቧል። የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ታገሰ ጫፎ በበኩላቸው፣ ኢትዮጵያዊያን አለመግባባቶችን በምክክር መፍትሔ ለመስጠት ጥልቅ ፍላጎት እንዳላቸው እስካሁን የተከናወኑ ተግባራት ያረጋገጡ መሆኑን ተናግረዋል ተብሏል።

## የመስክ ጉብኝት



በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የከተማ፣ መሠረተ ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የድሬዳዋ ዓለም ዓቀፍ ስታዲዮምን በጎበኘበት ወቅት

መስከረም 28 ወደ ድሬ ዳዋ የተጓዘው የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የከተማ፣ መሠረተ ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ በከተማይቱ አሥተዳደር እየተከናወኑ የሚገኙ መሠረተ ልማቶችን እና የአገልግሎት መስጫ ተቋማትን በመመልከት ብቸኛውን የወሩን የመስክ ጉብኝት አድርጓል። የኮሚቴው አባላት የድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጣናን፣ የደረቅ ወደብ እና ተርሚኑልን፣ የድሬ መሶብ የአንድ ማዕከል አገልግሎትን፣ ዓለም ዓቀፍ ስታዲዮሙን፣ የኮንቬንሽን ማዕከሉን እና የእመርታ ቤተ-መጽሓፍትን በመጎብኘት ከአሥተዳደሩ ከፍተኛ አመራሮች ጋር መወያይቱን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ፕሮፌሰር መሐመድ አብዶም፣ በድሬዳዋ እየተገነቡ የሚገኙ መሠረተ ልማቶች የነዋሪውን የልማት እና የአገልግሎት ጥያቄዎች በፍጥነት እና በጥራት እንዲመለሱ የሚያግዙ ናቸው ማለታቸውን መረጃው ጠቅሷቸዋል። የመሠረተ ልማቶቹ መገንባት ድሬዳዋን የኢንዱስትሪ፣ የንግድ እና የኮንፍረንስ ቱሪዝም ዘርፎች ተመራጭ አካባቢ እንደሚያደርጋት የጠቀሱት ፕሮፌሰሩ፣ በተለይ በቅርቡ አገልግሎት መስጠት የጀመረው መሶብ ድሬ የአንድ ማዕከል አገልግሎት እንቅስቃሴ አበረታች ነው ብለዋል ተብሏል። የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. እሸቱ ተመስገን በበኩላቸው፣ አሥተዳደሩ ገቢን አሟጦ በመሰብሰብ፣ ሕዝብን እና ድርጅቶችን አስተባብሮ የልማት ጥያቄዎችን ለመመለስ እያከናወናቸው የሚገኙት ሥራዎች በአርዓያነት የሚጠቀሱ ናቸው ብለዋል። ከቋሚ ኮሚቴው አባላት መካከል፣ የተከበሩ ፍቃዱ ጋሻው እና ወ/ሮ ታለፍ ፍትሕ አወቀ፣ በአመራሩ የተናበበ ቅንጅት የከተማ አገልግሎቶችን ለማዘመን እና መሠረተ ልማቶችን ለማስፋፋት የተጀመረው ጥረት በላቀ ደረጃ መቀጠል እንዳለበት መናገራቸውን ዘገባው ያመለክታል። የድሬዳዋ አሥተዳደር ምክትል ከንቲባ ሀርቢ ቡህ በበኩላቸው፣ ቋሚ ኮሚቴው በድሬዳዋ ተገኝቶ ያደረገው የመስክ ግምገማ በቀጣይ የተሻለ ሥራ ለመሥራት የሚያነቃቃ መሆኑን ገልፀዋልም ተብሏል።



# የእንደራሴዎቹ የውክልና ሥራ

የኢፌዲሪ እንደራሴዎች፣ ከሐምሌ እስከ መስከረም መጨረሻ ሳምንት ከሚያከናውኗቸው ተግባራት ዋናው የውክልና ሥራ እንደመሆኑ፣ እንደራሴዎቹ ወደ ‘ምርጫ ወረዳዎቻቸው በመሄድ የወከሏቸውን የማወያየት እና ጥያቄዎቻቸውን የመስማት ተግባራቸውን፣ ከሐምሌ ወር በመቀጠል በዚኹ ወርም ከውነዋል።

ይኽች የእንደራሴ ዕትም ሽፋን በሰጠችው ወርኃ መስከረም ላይም፣ ከ50 በላይ የሚሆኑ የመራጭ-ተመራጭ መድረኮች ሲካሄዱ፣ በአፋር፣ ኦሮሚያ፣ አማራ፣ ሲዳማ፣ ጋምቤላ፣ ቤኒ ሻንጉል ጉሙዝ እና ሶማሌ ውይይቶቹ የተካሄዱባቸው ክልሎች ነበሩ። እንደራሴዎቹ ባደረጉት ሰፊ የሕዝብ ውክልና ሥራ እና የልማት ምልከታ ክንውን ላይ ከተነሱት ጥያቄዎች መካከል ዋንኞቹ የነበሩት የመሠረተ ልማት ዕጦት፣ የሰላም እና ፀጥታ ጉዳዮች፣ የኑሮ ውድነት እና የመልካም አሥተዳደር ችግሮች ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ነበሩ። እንደራሴዎቹም፣ በተነሱት ጥያቄዎች ላይ ማብራሪያና ምላሽ ከመስጠታቸው ባለፈ፣ የፌዴራል እና የክልል አሥፈጻሚ አካላት ትኩረት እንዲሰጡ የማሳሰቡን ሥራ እንደሚሰሩ ብሪጅ ካሰባሰበችው መረጃ መረዳት ችላለች፡፡ ከዚኽ ዋንኛ የእንደራሴዎቹ ዓመታዊ ግብር ከሆነው የውክልን ሥራ መካከል፣ በዚኽ ወር ዕትሟ የተወሰኑትን የውክልና ሥራዎች አሳጥራ መዳሰስን መርጣለች።

## ኦሮሚያ ምን አለች?



የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባኤ የተከበሩ ወ/ሮ ሎሚ በዶ፣ የጨፌ ምክር ቤት አባል ወ/ሮ መሰረት ጉደታ እና በኦሮሚያ ክልል የምሥራቅ ሸዋ ዞን ምክትል አሥተዳዳሪ አቶ ጉታ ገዳ በጋራ የዱግዳ ወረዳ እና መቂ ከተማ ነዋሪዎችን ባወያዩበት ወቅት



በመስከረም ወር በኦሮሚያ ክልል በተለያዩ ዞኖች ወደ 20 የሚጠጉ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት በአብዛኛው ከጨፌ ኦሮሚያ አባላት እና ከአካባቢው አሥተዳደሮች ጋር በመሆን የሕዝብ ውክልና ጉብኝቶችን እና ውይይቶችን አድርገዋል። እነዚህ ውይይቶችም በአብዛኛው በሰላም፣ በመሠረተ ልማት እና በመልካም አሥተዳደር ችግሮች ላይ ሲያተኩሩ፣ እንደራሴዎቹም የኅብረተሰቡን ጥያቄዎች በዝርዝር መቀበላቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

የተከበሩ ሲ/ር አሚራ መሀመድ በምዕራብ ሐረርጌ ዞን፣ በዴሳ የሚገኘው የጤና አገልግሎት ክፍተቶች እንዲሻሻሉ አሳስበው፣ በአዳቡልቱ ወረዳ የተሰሩ የልማት ሥራዎች ደግሞ አበረታች መሆናቸውን ገልጸዋል ተብሏል። የተከበሩ ወ/ሮ ብርቄ ባሕሩ በሰሜን ሸዋ ዞን፣ ደብረ ሊባኖስ እና ያያ ጉለሌ ከኅብረተሰቡ ጋር በሰላም፣ በኢኮኖሚያዊ እና በማኅበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ውይይት ሲያደርጉ፤ የተከበሩ ወ/ሮ ራሄል ነገሮ በበኩላቸው በባኮ ከተማ አጠቃላይ ልማት፣ ሰላም እና ፀጥታ እንዲሁም በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ትኩረት አድርገው መወያየታቸው ታውቋል። በተመሳሳይም የተከበሩ ወይዘሮ ዘውድነሽ ቱሉ፣ የተከበሩ ወ/ሮ ዜይነባ ኑራ፣ የተከበሩ ዶ.ር. ሐጂ ከድር አብዱሌ እንዲሁም የተከበሩ ወ/ሮ አበቡ ደምሴ በአርሲ ዞን የቆዩ የመሠረተ ልማት ጥያቄዎች ብቻም ሳይሆኑ፣ የኑሮ ውድነት እና የሰላም ጉዳዮች በአስቸኳይ ምላሽ እንዲያገኙ በዝርዝር ማንሳታቸውን ዘገባዎቹ ያመለክታሉ።

ወደ ኢሉባቦር ዞን መቱ ከተማ ለደረሱት የተከበሩ ኡስታዝ ካሚል ሸምሱ፣ ነዋሪዎቹ ክልሉ ከፍተኛ የተፈጥሮ ሀብት ቢኖረውም አንድም ፋብሪካ ያለመኖሩን እና የሆስፒታል እጥረት መኖሩን አንስተውላቸዋል። በተመሳሳይ ወ/ሮ እታገኝ እሸቱን ጨምሮ በዚኹ ዞን ውይይት ያደረጉት እንደራሴዎች የመብራት፣ ኔትወርክ፣ መንገድ፣ ሆስፒታል፣ መድኃኒት አቅርቦት እና የኑሮ ውድነት ችግሮች እንዲፈቱ ጠይቀዋል ተብሏል። የተከበሩ አቶ ጆን አህመድ አባሚልኪ በጅማ ዞን ኦሞ ናዳ ምርጫ ክልል በነበራቸው ውይይት፣ የአሰንዳቦ ከተማ የንጹህ መጠጥ ውኃ እና የናዳ-ቦነያ 42 ኪ.ሜ. ‘ርዝማኔ ያለው መንገድ ከአገልግሎት ውጭ መሆን እንገብጋቢ ጥያቄያችን ነው ሲሉ ተወያዮቹ እንዳነሱላቸው ተሰምቷል።

በምዕራብ ወለጋ ዞን የተገኙት የተከበሩ ወ/ሮ ቤተልሔም መልካሙ በመሩት ሕዝባዊ ውይይት፣ በቅልቱ ካራ ወረዳ የመብራት፣ መንገድ፣ መድኃኒት እና የአምቡላንስ እጥረት እንዲሁም የማቃ ነጆ አሶሳ አስፋልት መንገድ ሥራ እንዲጀመር ኅብረተሰቡ ጠይቋል ተብሏል። የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባኤ የተከበሩ ወ/ሮ ሎሚ በዶ በበኩላቸው፣ በምሥራቅ ሸዋ ዞን በሚገኙት ዱግዳ ወረዳ እና መቂ ከተማ ተገኝተው፣ እንደ ህዳሴ ግድብ ባሉ አገራዊ ፕሮጀክቶች የተሰማውን ደስታ ገልጸው፣ ቀጣይ ሥራዎች ላይ ሕዝቡ አጋርነቱን እንዲያጠናክር ጥሪ ማስተላለፋቸው ተሰምቷል።

በተመሳሳይ የተከበሩ ወ/ሮ ፋንታዬ ለገሰ በምሥራቅ ባሌ ዞን ሰዌና ወረዳ አርሶ አደሮች በመስኖ እያለሙ ያሉትን የሙዝ፣ ፓፓያ፣ ሸንኮራ አገዳ እና ሌሎች ፍራፍሬዎችን ጎብኝተው አበረታተዋል ተብሏል። በሸገር ከተማ የተከበሩ ዶ.ር. እሸቱ ተመስገን በሰበታ፣ ገላን ጉዳ እና ፉሪ የመልካም አሥተዳደር እና የመሠረተ ልማት ችግሮቹ ትኩረት እንዲሰጣቸው ሲያነሱ፣ በምዕራብ ሸዋ ዞን ሆለታ ከተማ የተገኙት የተከበሩ ወ/ሮ አዲሷ አሰፋ በበኩላቸው፣ የሥራ አጥነት ችግርን ለመቅረፍ የኢንዱስትሪ ፓርክ እንዲገነባ ጥያቄ አቅርበዋል።

በዚኹ ወርኃ መስከረም፣ በምሥራቅ ሐረርጌ ዞን ደደር ወረዳ እና ከተማ አሥተዳደር የተገኙት የተከበሩ ዶ.ር. ኤልያስ አህመድ እና ወ/ሮ ፈሪዳ ሸምሱድን የአርሶ አደሩን የልማት ሥራዎች ጎብኝተው፣ አርሶ አደሮቹ የኮምፖስት ማዳበሪያን በመጠቀም ሙዝ፣ ዘይቱን እና አቮካዶ የመሳሰሉ የተለያዩ ፍራፍሬዎችን ማምረት መጀመራቸውን አበረታተዋል ተብሏል። በምዕራብ ሸዋ ዞን ጨሊያ ምርጫ ክልል የደረሱት የተከበሩ ወ/ሮ ዛራ መሐመድም ከነዋሪዎቹ ጋር ባደረጉት ውይይት፣ ነዋሪዎቹ መንግስት በሰላም፣ ፀጥታ፣ መሠረተ ልማት እና በመልካም አሥተዳደር ዙሪያ የጀመራቸው ሥራዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ መናገራቸው ተዘግቧል። ከዚኽ በተጨማሪም፣ የኑሮ ውድነት እና የሥራ አጥነት ችግሮች በእጅጉ አሳሳቢ በመሆናቸው መንግስት እንደ አገር ትኩረት ሰጥቶ እንዲሠራላቸው በአጽንኦት ጠይቀዋል ተብሏል።

## ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ምን ጠየቀች?

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የተለያዩ ዞኖችን የጎበኙት እንደራሴዎቹ ወ/ሮ መናህል ኢምራን፣ አቶ ሙባረክ ኤልያስ እና ወ/ሮ ባሂታ ባውዴ፣ ዋና ዋና የልማት እና የፀጥታ ጥያቄዎችን ከመራጮቻቸው ተቀብለዋል ተብሏል።

አቶ ሙባረክ ኤልያስ በሆሞሻ፣ መንጌ እና አሶሳ ዞን ባካሄዷቸው ጉብኝቶች፣ በፀጥታ ችግር ምክንያት ከአዲስ አበባ-ኦሮሚያ ወደ አሶሳ ያለው መንገድ መዘጋቱ ያስከተለውን ከፍተኛ የኑሮ ውድነት እና የትራንስፖርት እንግልት ጉዳይ ላይ ነዋሪዎች ልዩ ትኩረት እንዲሰጠው ጠይቀዋል ተብሏል። በመሠረተ ልማት ዘርፍም፣ በተለይም የሆሞሻ-ህዳሴ ግድብ አስፓልት መንገድ እንዲሰራ፣ የመብራት እና የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት እንዲሟላ፣ የመድኃኒት አቅርቦት እጥረት እንዲፈታ እና የቆሙ የፌዴራል ፕሮጀክቶች እንዲቀጥሉ የሚሉት በብዙዎቹ የመራጭ-ተመራጭ መድረኮች ላይ መንሳታቸውን ከምክር ቤቱ ያገኘነው መረጃ ይጠቁማል።

የተከበሩ ወ/ሮ መናህል ኢምራን በአሶሳ ከተማ ባደረጉት ውይይት፣ የኦሮሚያ-ቤኒ ሻንጉል ጉምዝ መንገድ መዘጋት የፈጠረውን ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ከነዋሪዎች ሲቀበሉ፤ ሴት ተወያዮቹ፣ የሴቶች የትምህርት እና የሥራ ዕድል እንዲፈጠር፣ ሴት የመንግስት ሠራተኞች የጤና መድህን ተጠቃሚ እንዲሆኑ እና ፆታዊ ጥቃቶችን የመከላከል ሥራ እንዲጠናከር ጠይቀዋል ተብሏል።

እንደራሴዎቹ ወ/ሮ መናህል እና አቶ ሙባረክ፣ በክልሉ ሪፈራል ሆስፒታል ያለመኖር ችግር ነዋሪዎችን ለከፍተኛ ወጪ እየዳረገ መሆኑን አንስተው፣ ሆስፒታል እንዲገነባ መጠየቃቸው ተዘግቧል። ከዚኽ በተጨማሪም፣ ወ/ሮ ባሂታ ባውዲ በመተከል ዞን ማንዱራ እና ዳንጉር ወረዳ፣ የመንገድ እና የቴሌ-ኮሙኒኬሽን ችግሮችን ጨምሮ ከእንጅባራ-ጉባ ያለው የአስፓልት መንገድ መዘግየትን ከማንሳታቸው ባለፈ፣ በጸጥታ ችግር የወደሙ የትምህርት እና የጤና ተቋማት ዳግም እንዲገነቡም ጥያቄ መቅረቡን መግለፃቸው ተሰምቷል።

## በአፋር ምን ምን ተነሳ?


የተከበሩ ወ/ሮ አሲያ አብዱልቃድር፣ የተከበሩ ዘሀራ ሁመድ እና አቶ አህመድ አብዱልቃድር በውይይቱ ላይ

በዚኽ ዕትም ሽፋን በሰጠነው ወርኃ መስከረም፣ በአፋር ክልል በተለያዩ ቀናት የፌዴራል እና የክልል ምክር ቤት አባላት በኦውሲ ረሱ ዞን በሚገኙ የዱብቲ እና የኮሪ ወረዳዎች የሕዝብ ውክልና ውይይቶችን አካሂደዋል።

በዱብቲ ወረዳ በተካሄደው ውይይት፣ እንደራሴዋ የተከበሩ አሲያ አብዱልቃድር እና የፌዴሬሽን ምክር ቤቱ አባል የተከበሩ ዘሀራ ሁመድን ጨምሮ የሚመለከታቸው የክልሉ አሥተዳደሪዎች በተሳተፉበት ውይይት፣ የአዋሽ ወንዝ ጎርፍ የሚያስከትለው ተፅዕኖ፣ የንጹሕ መጠጥ ውኃ አቅርቦት፣ የጤና ተቋማት አገልግሎት፣ የግብርና ግብዓት እጥረት፣ የኤሌክትሪክ ተደራሽነት እና የገበያ ትስስር የሚሉት ርዕሰ ጉዳዮች ከተነሱት መካከል ዋና ዋናዎቹ እንደነበሩ መረጃዎቹ አመልክተዋል። የምክር ቤት አባላቱ በወረዳው የተሰሩ የልማት ሥራዎችን አበረታተው ያልተፈቱ ችግሮች ላይ አመራሩ ትኩረት እንዲሰጥ ማሳሰባቸውም ተዘግቧል።

በኮሪ ወረዳ በተካሄደው ውይይትም፣ የተከበሩ አሲያ አብዱልቃድር፣ የክልሉ ምክር ቤት አባል እና የንግድ እና ገበያ ልማት ቢሮ ኃላፊ የሆኑት የተከበሩ አቶ አህመድ አብዱልቃድር መገኘታቸው ሲጠቀስ፣ ነዋሪዎቹም የውኃ፣ የትምህርት፣ የጤና እና የልማት ጥያቄዎችን አንስተዋል ተብሏል። የገበያ ልማት ቢሮ ኃላፊው አህመድ አብዱልቃድር፣ ለረጅም ጊዜ የሕዝብ ጥያቄዎች የነበሩት የኤሌክትሪክ አገልግሎት እና የኔትወርክ ችግር መፈታቱን እና ወደ ወረዳው ማዕከል የሚያስገባው የአስፓልት መንገድም በመጠናቀቅ ላይ መሆኑን ገልፀዋል ተብሏል። የኮሪ ወረዳ ዋና አሥተዳደር አቶ አባስ ሀሮ በበኩላቸው፣ የቀሩት የመሠረተ ልማት ጥያቄዎች ከክልሉ መንግስት እና ከባለድርሻ አካላት ጋር በመነጋገር ደረጃ በደረጃ ምላሽ እንደሚያገኙ መናገራቸው ተሰምቷል።

## ከአማራ የተሰማው

በዚኹ የዓመቱ የመጀመሪያ ወር ወደ አማራ ክልል የተጓዙት እንደራሴዎች፣ ወደተለያዩ ዞኖች በመሄድ ሰፋ ያሉ የሕዝብ ውክልና ሥራዎችን ማከናወናቸውን የምክር ቤቱ ዘገባ ያሳያል።

በደቡብ ወሎ ዞን የተገኙት የተከበሩ አቶ ኃብተ ማርያም መኮንን፣ የቆዩ እና በፌዴራል መንገዶች አሥተዳደር ተጀምረው የተቋረጡ የጊምባ-ተንታ-ደላንታ መንገድ እና የመብራት ሰብ-ስቴሽን ጥያቄዎች ምላሽ እንዲያገኙ ጠይቀዋል ተብሏል።

ወደ ኦሮሞ ብሔረሰብ አሥተዳደር ዞን የደረሱት የተከበሩ ወ/ሮ ከድጃ ያሲንም፣ በደዋ ጨፋ ምርጫ ክልል ያለው የኔትወርክ ዝርጋታ መፈታቱን እና አንዳንድ የኤሌክትሪክ መስመሮችም መሻሻላቸውን ቢገልጹም፣ ከሚሴ-ደዌ-መዳና-ባቲ አስፓልት መንገድ ግንባታን ጨምሮ ለረጅም ጊዜ ምላሽ ያላገኙ የልማት ፕሮጀክቶች

ከዚኽ ባለፈም፣ የተከበሩ አቶ አህመድ ሀሰን አዲስ የመብራት ዝርጋታ፣ የአስፓልት መንገድ፣ የኔትወርክ እና የመጠጥ ውኃ ብልሽት ጥገና ጥያቄዎች እንዲመለሱ ጠይቀው፣ ታጣቂዎች የሰላም ጥሪውን ተቀብለው በሰላም እንዲገቡ ነዋሪዎች የበኩላቸውን እንዲያበረክቱ ያሳሰቡት ደግሞ፣ በአርጡማ ፉርሲ ወረዳ በተገኙበት ወቅት እንደሆነ የምክር ቤቱ ዘገባ ይጠቁማል። በጅሌ ጥሙጋ ወረዳ እና ሰንበቴ ከተማ የደረሱት የተከበሩ አቶ አህመድ ሀሰን በበኩላቸ፣ ከተለያዩ የመሠረተ ልማት ክንውኖች ባለፈ፣ ሆስፒታልም እንዲገነባ የሚለው የኅብረተሰቡን ጥያቄ አቅርበዋል ተብሏል።

በተያያዘም የአማራ ክልል ተመራጭ እንደራሴዎች፣ በክልሉ ተዘጋጅቶ በነበረው የ25 ዓመት የአሻጋሪ ዕድገት እና የዘላቂ ልማት ፍኖተ ካርታ ዙሪያ ውይይት ያደረጉ ሲሆን፣ ዕቅዱ ችግርን የለየ እና የመፍትሔ አቅጣጫዎችን ያመላከተ መሆኑ ተገልጿል ተብሏል። እነዚኹ እንደራሴዎች በክልሉ ባከናወኑት የሕዝብ ውክልና ሥራ ወቅት የተነሱ የሕዝብ ጥያቄዎች ምላሽ በሚያገኙባቸው መንገዶች ላይ ከክልሉ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ ጋር ውይይት ማድረጋቸው ሲጠቀስ፣ የተከበሩ አቶ መስፍን ዳኜ ደግሞ በሕዝብ ውክልና ሥራ ወቅት በክልሉ ደረጃ መመለስ ያለባቸው 1 ሺሕ 782 የተጠቃለሉ ጥያቄዎች መቅረባቸውን አስታውቀው፣ የሰላም እና የፀጥታ መረጋገጥ ለፕሮጀክቶች ውጤታማነት ቁልፍ መሆኑን መግለፃቸውን ዘገባዎቹ ጠቅሰዋቸዋል።

## ከርዕሰ መስተዳድሩ ጋር. . .

በኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሲዳማ እንደራሴዎች፣ ከሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር አቶ ደስታ ሌዳሞ ጋር ውይይት አድርገዋል። እንደራሴዎቹም፣ ከዚኽ በፊት ከሕዝብ የቀረቡላቸውን ጥያቄዎች ለፌደራል ተቋማት እንዳቀረቡ ጠቁመው፣ የተሰጣቸውን ምላሽም አብራርተዋል ተብሏል።

## የሶማሌ ክልሉ መድረክ



የተከበሩ አቶ ከማል ሃሺ መሐሙድ እና የክልሉ ምክር ቤት አባላት በጅግጅጋ ከተማ ከሚገኙ የአካባቢው ምሁራን፣ የመንግሥት ሠራተኞች እና ነጋዴዎች ጋር ሲወያዩ

የኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና የምክር ቤቱ አማካሪ ኮሚቴ አባል የተከበሩ ከማል ሃሺ መሐሙድ፤ በምርጫ ጣቢያቸው ሲተ ዞን ደምበል ወረዳ የሚገኘውን መራጭ ኅብረተሰብ በልማት-ተኮር ጉዳዮች ዙሪያ ማወያየታቸው ተዘግቧል። ነዋሪዎቹም፣ ወደ ከተማዋ የሚያስገቡ መንገዶች እንዲጠገኑ፣ የኅርፍ መውረጃ ላይ ድልድይ እንዲሠራ፣ የመብራት መስመር ተሸካሚዎች ከእንጨት ወደ ጠንካራ ተሸካሚ እንዲቀየሩ እና የውኃ አቅርቦት እጥረት እንዲፈታ ጠይቀዋል ተብሏል።

ከዚኽ በተጨማሪም፣ በከተማዋ የንግድ እንቅስቃሴ ቢኖርም የባንክ አገልግሎት ስለሌለ ንግድ ባንክ እንዲከፈት የሚለው የቆየ ጥያቄ በአስቸኳይ ምላሽ እንዲያገኝ አበክረው ሲያነሱ፣ አቶ ከማልም ጥያቄዎቹን ለሚመለከታቸው አካላት እንደሚያቀርቡ ቃላቸውን መስጠታቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ጠቁሟል።

በዚኽ ብቻ ያላበቁት እንደራሴው ከማል ሃሺ እና የክልሉ ምክር ቤት አባላት፣ በጅግጅጋ ከተማ ከሚገኙ የአካባቢው ምሁራን፣ የመንግሥት ሠራተኞች እና ነጋዴዎች ጋር በትምህርት ጥራት ዙሪያ ሰፊ ውይይት አድርገዋል። በዋናነትም በ12ኛ ክፍል ውጤት ማሽቆልቆል ዙሪያ እንደ ዋና መንስዔነት፣ ከዚኽ ቀደም የነበረው ተማሪ ማሳለፍ አለብህ የሚለው ሥርዓት፣ የግብዓት እና የመምህራን እጥረት፣ የክትትል ማነስ እንዲሁም በተማሪዎች በኩል በትጋት አለማጥናት እና በማኅበራዊ ሚዲያ መጠመድ መነሳታቸውን ከዚያው መድረክ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል። ችግሩን ለመቅረፍ ምሁራኑ የአራቢ የትምህርት ድጋፍ ቡድን እና የሥነ-ምግባር ድጋፍ ቡድን እንዲቋቋሙ አቅጣጫ ያስቀመጡ ሲሆን፣ የምክር ቤት አባላቱም የሰው ኃይል እና የግብዓት አገዛ ለማድረግ እና የመማር ማስተማሩን ሂደት በተጠናከረ መልኩ ለመከታተል ቃል ገብተዋል ተብሏል።

## ወደ ጋምቤላ. . .

በዚኹ ወርኃ መስከረም፣ ወደ ተመረጡበት ጋምቤላ ክልል ማጃንግ ብሔረሰብ ዞን ጎደሬ ምርጫ ክልል የደረሱት እንደራሴው አቶ አሸኔ አስተን፣ በዚያው ዞን ባደረጉት የመራጭ-ተመራጭ ውይይት፣ በርካታ አፋጣኝ ምላሽ የሚሹ የልማት እና የመልካም አሥተዳደር ጥያቄዎች ቀርበውላቸዋል ተብሏል። ከነዚያ መካከል፣ በፌዴራል መንገዶች አሥተዳደር ተጀምሮ የተቋረጠው አበቦ-ሜጢ-ኮቢጦ ማዞሪያ መንገድ እንዲጠናቀቅ፣ በዞኑ ውስጥ ያሉት የውስጥ ለውስጥ መንገዶች እንዲሰሩ፣ የመብራት መቆራረጥ እና የኔትወርክ ተደራሽነት ጉድለቶች እንዲስተካከሉ የሚሉት ዋንኞቹ መሆናቸውን ዘገባዎቹ ጠቁመዋል።

በተጨማሪም ማኅበረሰቡ የሜጢ ጤና ጣቢያ ወደ ሆስፒታል ደረጃ ከፍ እንዲል፣ በሜጢ ከተማ ያልተጀመረው የኮሪደር ልማት እንዲጣራ፣ በየቦታው ያሉ ኬላዎች እንዲነሱ እና በጎደሬ ወረዳ የሚገኘው ጊዜ ያለፈበት የአረም ማጥፊያ መድኃኒት በአስቸኳይ እንዲወገድ ተጠይቋል ተብሏል። የተከበሩ አሸኔ በበኩላቸው፣ የዞኑ ዋና ከተማ ሜጢን የማሳደግ ሥራ አመራሩን እና ማኅበረሰቡን በጋራ ማቀናጀት እንደሚያሻ ገልጸው፣ ዞኑ ከፍተኛ የቡና ምርት ቢኖረውም የሚገባውን ገቢ እንዳያገኝ ያደረገውን የጥራት ችግር ለመፍታት በትኩረት መሥራት አስፈላጊ መሆኑን አበክረው ተናግረዋል ተብሏል።

## የእንደራሴዎቹ በጎ አድራጎቶች

እንደራሴዎቹ፣ በወርኃ መስከረም በ'የተመረጡባቸው የምርጫ ክልሎች ካከናወኗቸው የውክልና ሥራዎች ባለፈ፣ ለደረሱባቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች የቁሳቁስ እና የገንዘብ ድጋፎችንም አበርክተዋል። ለማሳያ ያህልም፤ በአማራ ክልል ምሥራቅ ደምቢያ ወረዳ የተከበሩ ወ/ሮ ደብሪቱ ታደገ ለተማሪዎች የመማሪያ ቁሳቁስ ድጋፍ ሲያደርጉ፣ የተከበሩ ወ/ሮ ራህመት አወልም በደቡብ ወሎ ዞን ውስጥ ለሚገኙ ለረዳት ለሌላቸው ተማሪዎች፣ ለአቅመ ደካሞች እና ለተፈናቃዮች 9 ሚሊዮን ብር የሚገመት የትምህርት ቁሳቁስ እና የአልባሳት ድጋፎችን ማድረጋቸውን ከእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ያገኘነው መረጃ ያትታል። ወደ ኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ሸዋ ዞን ቦሰት፣ ፈንታሌ ወረዳ እና መተሐራ ከተማ ወርደው የነበሩት ሌላይኛው እንደራሴ የተከበሩ አቶ ሹሚ አያኖ በበኩላቸው፣ ከ700 በላይ ለሚሆኑ የአቅመ ደካማ እና የሚሊሻ ቤተሰብ ተማሪዎች ደብተር፣ እስክርቢቶ እና አልባሳት ከማበርከታቸው ባለፈ፣ ለኹለቱ ወረዳዎች እና ለከተማ አሥተዳደሩ ቢሮዎችም ወንበሮች፣ ጠረጴዛዎች፣ ኮምፒውተሮች እና ፕሪንተሮችን ጨምሮ የቢሮ መገልገያ ቁሳቁሶችን አበርክተዋል ተብሏል። በምሥራቅ ሸዋ ዞን ቦራ ወረዳም፣ በተከበሩ አቶ ጫላ ለሚ አስተባባሪነት ከ150 በላይ ለሚሆኑ የአቅመ ደካማ እና የሚሊሻ ቤተሰብ ልጆች የትምህርት ቁሳቁሶች ድጋፍ መደረጉ ተዘግቧል። ወደ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ሀላባ ዞን ብቅ ባሉት የተከበሩ ዶ.ር. ነጃት ግርማ ጠያቂነት፣ የነጻነት የሕፃናት ማሳደጊያ በጎ አድራጎት ድርጅት ለ30 የዕድገት ውስንነት ላለባቸው ሕፃናት ከ100 ሺሕ ብር በላይ ግምት ያለው አልሚ ምግብ ድጋፍ መደረጉ ታውቋል።

# የፓርላማ ዲፕሎማሲ

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ በአዲሱ ዓመት ወርኃ መስከረም፣ ሦስት ፓርላመንታዊ የዲፕሎማሲ ሥራዎችን ከውኗል።





በቀዳሚነት ሊጠቀስ የሚችለው፣ የኢትዮ-ኩባ ወዳጅነት ቡድን አባላት ከኩባ ሕዝባዊ የወዳጅነት ተቋም ፕሬዝደንት እና ከኩባ ፓርላማ አባል የተከበሩ ሚስተር ፈርናንዶ ጎንዛሌዝ ሎርት ጋር የተካሄደው ውይይት ሲሆን፣ በውይይቱም የኢትዮ-ኩባ ወዳጅነት ቡድን አባላቱ በኹለቱ አገራት መካከል ያለውን የትብብር እና የጋራ ዓላማዎችን የበለጠ ለማጠናከር እንደሚሰሩ ተመክሯል ተብሏል። በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የኢትዮ-ኩባ ወዳጅነት ሊቀመንበር የሆኑት የተከበሩ ዶ.ር. አብዱልቃድር ገልገሎ፣ ኢትዮጵያ ከኩባ ሪፐብሊክ መንግሥት ጋር ረጅም ዘመን ያስቆጠረ ታሪካዊ ወዳጅነት ያላት አገር መሆኗን አስታውሰው፣ በቀጣይም የኹለትዮሽ ግንኙነቶችን ለማጠናከር ባላት ቁርጠኝነት አዳዲስ ትብብርን ለመፍጠር በትኩረት ትሰራለች ብለዋል ተብሏል። የኩባው እንደራሴ እና የኩባ ሕዝባዊ የወዳጅነት ተቋም ፕሬዝዳንት የተከበሩ ሚስተር ፈርናንዶ ጎንዛሌዝ ሎርት በበኩላቸው፣ ኢትዮጵያ እና ኩባ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ከጀመሩ 50 ዓመታት እንደሞላቸው አስታውሰው፣ እስካኹንም ኹለቱ አገራት ትኩረት በሚሹ ዋና ዋና መስኮች በተለይም በሳይንስ ና ቴክኖሎጂ፣ በትምህርት፣ በግብርና ቴክኖሎጂ፣ በባህል፣ በኢኮኖሚያዊ ትስስር፣ በስፖርት እና ቱሪዝም እንዲሁም በሌሎችም ዘርፎች ዙሪያ ሥራዎችን እየሠሩ መሆናቸውን መናገራቸውን ዘገባው ጠቅሷቸዋል።

በመስከረም ወር እንደራሴዎቹ የከወኑት ኹለተኛው ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የኢትዮ-ምዕራብ ኤዥያ ወዳጅነት ቡድን አባላት፣ ከሳዑዲ ዐረቢያ የፐብሊክ ዲፕሎማሲ አባላት ጋር የተወያዩበት መድረክ ነበር። የኢትዮ-ምዕራብ ኤዥያ ወዳጅነት ቡድን ሰብሳቢው የተከበሩ ሙሐመድ አል አሩሲ፣ ኢትዮጵያ እና ሳዑዲ አረቢያ ረጅም ዓመታትን ያሰቆጠረ ታሪካዊ ግንኙነት እና የጋራ ባህል እንዳላቸው አውስተው፣ ኹለቱ አገራት ከኹለትዮሽ ግንኙነት በተጨማሪ በባለብዙ ወገን ትብብርን ለማጠናከር በሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ በጋራ እየሰሩ መሆኑን ጠቁመዋል ተብሏል፡፡ ሌላይኛው የቡድኑ አባል የተከበሩ መስከረም ኃይሉ በበኩላቸው፣ በኢትዮጵያ እና በሳዑዲ ዐረቢያ መካካል ያለው ግንኙነት አበረታች መሆኑን ጠቁመው፣ የፐብሊክ ዲፕሎማሲ አባላቱ ወደ ኢትዮጵያ የመጡት ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በኢትዮጵያ ሕዝብ እና መንግስት በጋራ የራስ ጥረት ግንባታው ተጠናቆ በተመረቀበት ማግስት በመሆኑ ልዩ እንደሚያደርገው መጥቀሳቸው ተሰምቷል። የሳዑዲ ዐረቢያ የፐብሊክ ዲፕሎማሲ አባላት በበኩላቸው፣ ስለ ኢትዮጵያ የሰማነው እና በተግባር የተመለከትነው ነገር የተለያየ ነው ማለታቸው ሲሰማ፤ ኢትዮጵያ በፈጣን እድገት እና በለውጥ ጎዳና ላይ የምትገኝ፣ ለቱሪስቶች ምቹ የሆነች፣ ሕዝቧም እንግዳ ተቀባይ፣ በመከባባር እና በመቻቻል የሚኖር መሆኑን በተግባር በተለያዩ የአገሪቱ ክፍል ተዘዋውረው መመልከታቸውን ለኢትዮጵያውያኑ አቻዎቻቸው ገልፀውላቸዋል ተብሏል።



በኢፌዴሪ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የውጭ ግንኙነት እና ሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የኢትዮ-ስዊድን የፓርላማ የወዳጅነት ቡድንን ተቀብሎ ባነጋገረበት ወቅት

ሦስተኛው የወሩ የፓርላማ ዲፕሎማሲ ክንውን በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የውጭ ግንኙነት እና ሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የኢትዮ-ስዊድን የፓርላማ የወዳጅነት ቡድን ተቀብሎ ማነጋገሩ ነበር። በዚያ ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ ክንውን ወቅትም፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የውጭ ግንኙነት እና ሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ ዶ.ር. ዲማ ኖጎ፣ ኢትዮጵያ ከስዊድን ጋር ጠንካራ እና ታሪካዊ የሆነ ግንኙነት እንዳላት ጠቅሰው፣ ይኸ ትብብር በመከላከያ፣ በግብርና እና በትምህርት ዘርፎች ለብዙ ዐሥርት ዓመታት የዘለቀ እንደሆነም አንስተዋል ተብሏል። ይኹን እንጂ የአውሮፓ ኅብረት በቅርቡ በኢትዮጵያውያን ዜጎች ላይ የጣለው የቪዛ ገደብ የኹለቱን አገራት የኹለትዮሽ ግንኙነት ሊጎዳ እንደሚችል ስጋታቸውን በማንሳት፣ ስዊድንም ይኽን ገደብ ለማስነሳት የበኩሏን እንድትወጣ መጠየቃቸውን ዘገባው ጠቅሷቸዋል።

የኢትዮ-ስዊድን የፓርላማ የወዳጅነት ቡድን ኃላፊው የተከበሩ መግኑስ ኦስከርሶ በበኩላቸው፣ ውይይቱ በኹለቱ አገራት የነበረውን የረዥም ዓመታት አጋርነት የበለጠ ለማጠናከር እና ትብብራቸውን ለማሳደግ በሚያስችሉ መንገዶች ላይ ምክክር ለማድረግ ያለመ መሆኑን ተናግረዋል። ልዑካን ቡድኑ ኢትዮጵያ የስንዴ እና የምግብ ምርትን በማሳደግ ያስመዘገበችውን ውጤት አድንቀው፣ የአገሪቱን ወቅታዊ የጸጥታ ኹኔታ ለመረዳት ያስቻለ እንደነበርም መጥቀሳቸው ተዘግቧል።

# እንደራሴዎቹ ስለ‘ራሳቸው በ‘ራሳቸው

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ምክር ቤት ወርኃ መስከረምን ያሳለፉት ከላይ የዳሰስናቸውን ሕገ-መንግሥታዊ ኀላፊነቶችን በመከወን ብቻም ሳይሆን፣ የምክር ቤታቸውን የሪፎርም ኮሚቴ ግምገማ፣ የክረምት የውክልና ሥራ አፈጻጸም ግምገማ እና የምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት የአመራር አባላት የምክር ቤቱን የመክፈቻ የዝግጅት አስመልክቶ ያቀረቡትን ሪፖርት መገምገምን የጨመሩ ክንውኖችን በመፈጸም እና የእንደራሴዎቹን ቴሌቪዥንም በማስጀመር ነበር።



የሪፎርም ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ አቶ መለሰ መና

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የሪፎርም ኮሚቴ፣ የምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት ለያዝነው ዓመት የምክር ቤቱ መክፈቻ ሥርዓት ያደረገውን የኹለት ወራት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ከከፍተኛ አመራሮች ጋር በመሆን የገመገመበት ኹነት ቀዳሚው የወሩ የ‘ራስ በራስ የእንደራሴዎቹ ክንውን ነብር። የጽሕፈት ቤቱ የዋና ጸሓፊ ተወካይ ተወካይ አቶ ከረዮ ባናታ ባቀረቡት ሪፖርት፣ ጽሕፈት ቤቱ በተለይ በሰው ሀብት አሥተዳደር እና በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዘርፎች ላቅ ያለ ሥራ መሥራቱን ገልጸዋል ተብሏል። ኀላፊው አክለውም፣ በአዲሱ አደረጃጀት መሰረት ሠራተኞች ሥራ መጀመራቸውን፣ የተፈጠሩ የሥራ መደቦች ክፍተቶችንም በማስታወቂያ ለመሙላት እየተሰራ መሆኑን እና የሠራተኞችን አቅም ለማሳደግ ሥልጠናዎች መሰጠታቸውን ጠቁመዋል። በተጨማሪም የግዥ፣ የፕሮቶኮል እና የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት ሥራዎች በሚገባ መከናወናቸውን አስረድተው፣ በተቋሙ የግንባታ ፕሮጀክቶች ላይ መጓተት መኖሩን እንደ ክፍተት ማንሳታቸውን የምክር ቤቱ ዘገባ ይጠቅሳል።

የሪፎርም ኮሚቴው በበኩሉ፣ ጽሕፈ ቤቱ ያቀረበውን ሪፖርት ከመረመረ በኋላ አፈጻጸሙን ከማድነቁ ባለፈ፣ ጽሕፈት ቤቱ ተግባርን በመቁጠር የሚያቅድ እና የሚፈጽም ተቋም እየሆነ መምጣቱን አንስቶ፣ ከዚኽ በፊት በሰው ኃይል ዙሪያ የነበሩ ችግሮች እየተቀረፉ መሆኑን ገልጿል ተብሏል። የኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ አቶ መለሰ መና በበኩላቸው፣ ሰራተኛውን በማሰልጠን እና የሚገባው ቦታ ላይ በመመደብ የተሰራው ሥራ፣ የተሻሻለው የግዥ አፈጻጸም እንዲሁም በቴክኖሎጂ የተደገፈው የውክልና ሥርዓት የሚበረታቱ መሆናቸውን ጠቅሰዋል። የምክር ቤቱ የሚዲያ ሽፋን ጥሩ ደረጃ ላይ መድረሱንም ሰብሳቢው አክለዋል ተናግረዋል

ሌላኛው የእንደራሴዎቹ የ‘ራስ በ‘ራስ ክንውን፣ 6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የ2017 የክረምት የሕዝብ ውክልና ሥራ ግምገማ ሲሆን፤ በክረምት የውክልና ሥራ ምን ምን ሥራዎች እንደተሰሩ፣ በሥራ ሂደቱ የተገኙ ውጤቶች፣ ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ የመፍትሔ አቅጣጫዎች ምን እንደሚመስሉ የሚሉት ትኩረት የተሰጣቸው የመወያያ ርዕሰ-ጉዳዮች እንደነበሩ፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የመንግስት ረዳት ተጠሪ ሚኒስትር ዴኤታዋ ወ/ሮ መሠረት ኃይሌ አብራርተዋል።




የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ፣ ምክትል አፈ ጉባኤዋ እና በምክር ቤቱ የመንግስት ተጠሪው፣ የእንደራሴዎቹን ቴሌቪዥብ ጣቢያ መርቀው በከፈቱበት ወቅት

የወሩ የመጀመሪያ ዓመት ሌላይኛው ዋንኛ ክንውን ተብሎ ሊጠቀስ የሚችለው የእንደራሴዎቹ ግብር፣ ረዘም ላሉ ዓመታት ሲጠበቅ የነበረውን የምክር ቤቱን የቴሌቪዥን ጣቢያ መክፈት ነበር። ይኸው ኢቢሲ ፓርላማ ቲቪ የተሰኘው ጣቢያ፣ መስከረም 26 2018 ዓ.ም. ተመርቆ ሥራውን በይፋ ጀምሯል፡፡ በምርቃ ሥነ-ሥርዓቱም ላይ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ የተከበሩ አቶ ታገሰ ጫፎ፣ የምክር ቤቱ ምክትል አፈ-ጉባኤ ወ/ሮ ሎሚ በዶ፣ የመንግስት ዋና ተጠሪ ሚኒስትሩ የተከበሩ ዶ.ር. ተስፋዬ በልጅጌ፣ የቋሚ ኮሚቴዎች ሰብሳቢዎች እና ሌሎች ተጋባዥ እንግዶች ተገኝተው እንደነበር የምርቃው ዘገባ ያሳያል፡፡



የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ኢቲቪ ፓርላማ ስርጭት ለመጀመር ላለፉት ዓመታት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ዝግጅት ሲያደርግ መቆየቱን የጠቀሱት አፈ ጉባኤው ታገሰ ጫፎ፣ የኢቲቪ ፓርላማ ቻናል ስርጭት የሕዝብ ተሳትፎ እና የዴሞክራሲ ባህልን ያሳድጋል ብለዋል ተብሏል፡፡ አፈ ጉባኤው አክለውም፣ ስርጭቱ በአገሪቷ ላይ የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች እና የተለያዩ እቅዶችን በምንገመግምበት ጊዜ የሕዝቡን ጥያቄ እና ቅሬታ በቀጥታ እንድናስተላልፍ እና መፍትሔው ላይ በትኩረት እንድንሰራ ያስችለናልም ብለዋል። የቴሌቪዥን ቻናሉ ሕዝብ እና ምክር ቤቱ መረጃ የሚለዋወጡበት እና ለጠንካራ አገረ መንግስት ግንባታ የራሱን ድርሻ ለመወጣት ያስችላል ያሉት ደግሞ የመንግስት ዋና ተጠሪ ሚንስትሩ የተከበሩ ዶ.ር. ተስፋዬ በልጅጌ ሲሆኑ፣ ጣቢያው የምክር ቤቱን የሕግ አወጣጥ ሂደትን፣ በምክር ቤቱ የሚወሰኑ ውሳኔዎችን እና የሕዝብ ውክልና ሥራዎችን አፈፃፀም ለሕዝብ ለማቅረብ አጋዥ ሚና የሚጫወት መሆኑንም አክለው መናገራቸው ተዘግቧል፡፡ ምክትል አፈ ጉባኤዋ ሎሚ በዶ በበኩላቸው፣ ኢቲቪ ፓርላማ ቻናል ሥራውን በይፋ መጀመሩ የዲሞክራሲ ሥርዓትን ለማስፈን እና ለማስረፅ ሚናው የጎላ መሆኑን በመጥቀስ፣ ምክር ቤቱ የራሱን ቻናል እንዲኖረው መደረጉ የምክር ቤቱን ተልዕኮዎች ለሕዝብ ተደራሽ ለማድረግ ዘርፈ ብዙ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ጠቁመዋል፡፡

በምርቃት ሥነ ሥርዓቱ ላይ የተገኙንት የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ኮሚሽነር ክቡር ብርሃኑ አዴሎም፣ የኢቲቪ የቻናሉ መከፈት ፓርላማው ካለው ትልቅ ኃላፊነት አንጻር ለኅብረተሰቡ የበለጠ ቅርብ እንዲሆን የሚያስችለው ትልቅ ስኬት እንደሆነ ሲያነሱ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ዋና ዕንባ ጠባቂ ክብርት ወይዘሮ ስመኝ ውቤም፣ የዲሞክራሲ ተቋማት በቀላሉ ለኅብረተሰቡ ተደራሽ እንዲሆኑ በማስቻል በተለያዩ ተቋማት የሚፈጸሙ የመልካም አሥተዳደር ችግሮች እልባት እንዲያገኙ ያስችላል ብለዋል ተብሏል።



# የብሪጅ ዕይታ በስምምነቱ ሰነድ ዙሪያ

የወርኃ መስከረም የብሪጅ ዳሰሳዊ ምልከታ ማተኮሪያ ርዕሰ-ጉዳይ፣ ተቋማችን ብሪጅ ሪሰርች እና ኢኖቬሽን፣ ከእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት ጋር በጋራ ለመሥራት የሚያስችላቸውን ስምምነት የመፈራረማቸው አንዱ የወሩ ዋንኛ ክንውን እንዲሆን ተመርጧል።

የኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት፣ ከብሪጅ ሪሰርች ጋር በጋራ ለመሥራት የሚያስችለውን የስምምነት ሰነድ ተፈራራሚዎች፣ የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት ዋና ጸሓፊ ተወካይ አቶ ከረዮ ባናታ እና የብሪጅ ሪሰርች እና ኢኖቬሽን ዳይሬክተር ዶ.ር. ቃለአብ ታደሰ ሲሆኑ፤ በስምምነቱ ከተካተቱት ርዕሰ-ጉዳዮች መካከልም፣ ለእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የምርምር ድጋፎችን ማድረግ፣ የአቅም ግንባታ ሥልጠና መስጠት እና የምክር ቤቱን ሥራዎች ለሕዝብ ለማቅረብ የሚያስችሉ ተግባራትን ማከናወን የሚሉት ዋንኞቹ የስምምነቱ ፍሬ ይዘቶች መሆናቸው ታውቋል። በስምምነቱ ላይ የተገኙት የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባኤዋ የተከበሩ ሎሚ በዶ፣ በስምምነት ሰነዱ የተካተቱት የትብብር መስኮች እና ዝርዝር አፈፃፀማቸው ከምክር ቤቱ ተልዕኮ አንፃር ተገናዝቦ ሰነዱ ለሣስት ወራት በጥልቀት ታይቶ ተቀባይነት ማግኘቱን ገልፀዋል። አፈ ጉባኤዋ አክለውም፣ ከበጀት እና አሥተዳደር ጋር ያሉ ጉዳዮች በአፅንኦት መታየታቸውን አመልከተዋል። ከአፈ ጉባኤዋ ባለፈም፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የጽሕፈት ቤቱ ዋና ጸሓፊ ተወካይ አቶ ከረዮ ባናታ፣ ጽሕፈት ቤቱ ከብሪጅ ጋር በመተጋገዝ በምርምር፣ በአቅም ግንባታ እና በተያያዥ ጉዳዮች ላይ በጋራ እንደሚሰራ መናገራቸውን እንደራሴ ተረድታለች።

በብሪጅ ሪሰርች እና ኢኖቬሽን የማኅበረሰብ ድርጅት የቦርድ ሰብሳቢዋ እና የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሰላም እና ደህንነት ተቋም ዳይሬክተሯ ዶ.ር. ሜርሲ ፍቃዱ በበኩላቸው፣ ስምምነቱ በብዙ ውይይቶች መካከል ያለፈ፣ ቀጣይነትን የሚያመላክት እና ለረዥም ጊዜ ታስቦ የተዘጋጀ መሆኑን ጠቁመው፣ በውል ስምምነቱ ከተገለፁ ሥራዎች በተጨማሪ በሂደት የታሰቡ ሥራዎች መኖራቸውን ገልፀዋል። ዶ.ር. ሜርሲ አክለውም፣ ብሪጅ የማይቋረጥ አገልግሎት ለመስጠት መዘጋጀቱን እና በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ተግባር እንደሚገባም በዚያ ዕለት ሲናገሩ ተደምጠዋል። የብሪጅ ዳይሬክተር ዶ.ር. ቃለአብ ታደሰ፣ የመግባቢያ ሰነዱ በብሪጅ ተቋማዊ ተልዕኮ ውስጥ ትልቅ ምዕራፍ መሆኑን አስምረውበታል። ይህ ስምምነት የተለመደ ተቋማዊ አጋርነት ብቻ አይደለም ያሉት ዳይሬክተሩ፣ በኢትዮጵያ ኹለንተናዊ ዴሞክራሲ እና ልማዊ እድገት አስተዋጾ የሚያደርጉ ጠንካራ የጥናትና ምርምር ተቋማት እንዲኖሩ የተሰነቀ የጋራ ራዕይ ነውም ሲሉ ርዕያቸውን ለመጽሔታችን አጋርተዋል።

በዕለቱ፣ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት የሙያዊ ዘርፍ ምክትል ዋና ጸሐፊውን ዶ.ር. ንጉሤ መሸሻን ጨምሮ፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የመንግስት ተጠሪ ጽሕፈት ቤት ኃላፊው አቶ አንድነት አድነው መገኘታቸውን ተገንዝበናል።

## የብሪጅ ነገዎች

በተቋማችን ብሪጅ እና በእንደራሴዎቹ ጽሕፈት ቤት መካከል ስምምነት የተደረሰበት የመግባቢያ ሰነድ፣ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትን ተቋማዊ አቅም እና ዲሞክራሲያዊ ውጤታማነት በቀጥታ የሚደግፍ፣ እንዲኹም በምርምር፣ በሥልጠና እና በሕዝብ ተሳትፎ መጎልበት ላይ የሚያተኩር የረጅም ጊዜ የትብብር ማዕቀፍ እንደሚያስቀምጥ ብሪጅ መረዳት ችላለች። ስምምነቱ ሰፋ ያሉ የትብብር ማዕቀፎችን ያቀፈ ሲሆን ከእነዚህም መካከል ዋንኞቹ የሚከተሉት ናቸው።

- **በማስረጃ ላይ የተመሰረቱ ፖሊሲዎችን እና የሕግ አወጣጥ ሂደቶችን በተጨባጭ እና ወቅት ተኮር ምርምሮች መደገፍ፤**
- **ለእንደራሴዎቹ እና ለምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት ባልደረቦች በተመረጡ ርዕሰ-ጉዳዮች ላይ የአቅም ግንባታ ሥልጠና መስጠት፤**
- **የምክር ቤቱን የአሥራር ሥርዓት ግልፅነትን የሚያጎለብቱ እና ምክር ቤቱ የተለያዩ ሕገ-መንግሥታዊ ተግባራቱን ለሕዝብ የሚያስተላልፍበትን መንገድ የሚያሻሽሉ የመረጃ መጋራት ተግባራትን መደገፍ እና ማሳለጥ እንዲሁም፤**
- **ለጠንካራ ዲሞክራሲያዊ ተቋማት የጋራ ራዕይን መተግበር የሚሉት መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል።**



የተከበሩ ምክትል አፈ-ጉባኤ ወ/ሮ ሎሚ በዶ ከጽሕፈት ቤቱ ኃላፊዎች
እና ከብሪጅ ሪሰርች አመራሮች ጋር ውይይት ሲያደርጉ



የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የዋና ጸሓፊ ተወካይ እና የአሥተዳደር ዘርፍ ምክትል ዋና ጸሐፊው አቶ ከረዩ ባናታ
እና የብሪጅ ሪሰርች እና ኢኖቬሽን ዋና ዳይሬክተር ዶ.ር. ቃለአብ ታደሠ የመግባቢያ ሰነዱን በተፈራረሙበት ወቅት

ብሪጅ ሪሰርች ኤንድ ኢኖቬሽን በዋናነት የእንደራሴዎች ምክር ቤቶች ላይ ትኩረት አድርጎ ጥናት እና ምርምር የሚያደርግ ሀገር በቀል ድርጅት ነው፡፡ በሌሎች አገራት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤቶችን ተግባራት በተመለከተ ለዜጎች ግንዛቤ የሚሰጡ እና በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤቶች ላይ ብቻ ትኩረት በማድረግ ጥናት እና ምርምር የሚያደርጉ ተቋማት አልያም ለምክር ቤቶቹ ጥናታዊ ምርምሮቻቸውን ተንተርሰው ሙያዊ ድጋፍ የሚያደርጉ ድርጅቶች በሰፊው ይታወቃሉ። ብሪጅ ሪሰርች ኤንድ ኢኖቬሽንም፣ በዚኽ ረገድ በአገራችን የሚገኙ የፌደራል እና የክልል ምክር ቤቶችን እና በምክር ቤቱ ውስጥ የሚገኙ ቋሚ ኮሚቴዎች ዘወትራዊ ሕገ-መንግሥታዊ ክንውኖቻቸውን እና ተግባራቶቻቸውን በመከታተል፣ ማኅበረሰቡ ስለ ምክር ቤቶቹ ወቅታዊ ተግባራት ተገቢው መረዳት እንዲኖረው ዋነኛ የትኩረት ማዕቀፉ አድርጎ ለመሥራት ተቋቁሟል።

ለዚኽ ግብ መሳካትም፣ በቀዳሚነት ጥልቀት ያላቸው እና በተጨባጭ መረጃ የተደገፉ ወቅታዊ እና ዘላቂ ምርምሮችን በማከናወን ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ ለምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች እና ለምክር ቤቶቹ ጽሕፈት ቤቶች ግብዓት የሚሆኑ የምርምር ሥራዎችን ያከናውናል፤ በምርምር ውጤቶቹ ታግዘም ተቋማቱ ኅላፊነቶቻቸውን በተሻለ መልኩ እንዲወጡ ሥልጠና ተኮር ድጋፎችን ያደረጋል። ከዚኽ ባለፈም፣ ብሪጂ ሪሰርች ኤንድ ኢኖቬሽን፣ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤቶች በቀጥታ በሚመለከቷቸው ርዕሰ-ጉዳዮች ዙሪያ፣ በመልካም አሥተዳደር፣ በሠላም እና ሰዋዊ ልማት ተኮር ጉዳዮች የተሰማሩ ባለድርሻ አካላት የሚወያዩባቸው እና ሐሳብ የሚለዋወጡባቸው ሕዝባዊ መድረኮችን በማዘጋጀት ለአገሪቷ ዲሞክራሲያዊ ተቋማት መጎልበት የበኩሉን ድርሻ ይወጣል። በተጨማሪም፣ እንደራሴዎች፣ የተለያዩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የሲቪል ማኅበረሰቡ አባላት እና ሌሎች የሚመለከታቸው መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት በመልካም አሥተዳደር፣ በሰላም ግንባታ እና ማኅበረሰባዊ ልማት ላይ የተሰማሩ ባለድርሻ አካላትን አቅም ለማጎልበት የሚረዱ የሥልጠና መድረኮችን ያዘጋጃል፡፡

# አላማ

የብሪጅ ሪሰርች ኤንድ ኢኖቬሽን ቀዳሚ አላማዎች የሚከተሉት ናቸው፤

1. **የሕዝብ ተወካዮች ተቋማት በተለይም የኢፌዲሪ የእንደራሴዎች ምክር ቤት በማኅበረሰቡ ዘንድ ያለውን ተደራሽነት እና ገጽታ በማሳደግ፣ ማኅበረሰቡ ስለ ተቋማቱ እና ምክር ቤቱ ሕገ-መንግሥታዊ ተግባራት የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖረው የሚያስችሉ ሥራዎችን መሥራት፤**
2. **የሕዝብ ተወካዮች ተቋማትን እና የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎችን ሕገ-መንግሥታዊ ተግባራት የሚያግዝ ጥናት እና ምርምር ማካሄድ፣ ትንታኔዎችን ማዘጋጀት፣ ማሰራጨት፣ ሥልጠና መስጠት እና ተጨባጭ ምርምሮች ላይ የተንተራሱ የትግበራ አቅጣጫዎችን መጠቆም፤**
3. **ኢትዮጵያ የምትመኘውን የበለጸገ ኢኮኖሚ፣ አንድ የፖለቲካ ማኅበረሰብ እና የጎለበተ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን የሚያንጸባርቅ ጠንካራ የእንደራሴዎች ምክር ቤት እንዲኖር ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ፤**
4. **ዜጎች በሠላም፣ በመልካም አሥተዳደር እና በልማት ጉዳዮች ላይ የሚወያዩባቸው እና ሐሳብ የሚለዋወጡባቸው የውይይት መድረኮችን ማዘጋጀት፤**
5. **ለፖሊሲ አውጪዎች፣ ለዲሞክራሲ ተቋማት፣ በተለያዩ የፌደራል እና የክልል የአሥተዳደር ዕርከን ላይ ለሚገኙ የሥራ ኃላፊዎች የሚበጁ የጥናት እና የምርምር ሕዝባዊ መድረኮችን ማዘጋጀት እና፤**
6. **በሠላም፣ በአሥተዳድር፣ እና በልማት ጉዳዮች ላይ የሴቶችን፣ የአካል ጉዳተኞችን፣ አናሳ ድምጽ ያላቸውን እና ሌሎች ድጋፍ የሚፈልጉ የማኅበረሰብ ክፍሎችን ተሳትፎ ማሳድግ የሚሉት ይገኙበታል፡፡**

## ተቋማዊ አቅጣጫዎች

- ጨባጭ ምርምሮች እና ፖሊሲ ተኮር ትንተናዎችን ማከናወን፤
- የሕዝብ እንደራሴዎች ሕገ-መንግሥታዊ ሥራዎችን መከታተል፤
- በተለያዩ ርዕሰ-ጉዳዮች ላይ የሚካሄዱ የአቅም ግንባታ ተግባራት፥- የተነጠሉ ርዕሰ-ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ የአንድ ዙር ሥልጠናዎችን መስጠት፤
- ከተለያዩ ዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ ርዕይ ዙሪያ ትብብር የመፍጠር ተግባራት፤
- ዓለም ዓቀፋዊ፣ አህጉራዊ እና ቀጠናዊ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ሙያዊ ትንተናዎችን ለእንደራሴዎቹ ማቅረብ፤
- የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ ማጎልበት እና፤

## አኹናዊ የብሪጅ ሪሰርች ኤንድ ኢኖቬሽን ተግባራት መደበኛ ኅትመቶች

- “እንደራሴ” የተሰኘች፣ የኢፌዲሪ የእንደራሴዎች ምክር ቤትን የየወሩ ሕገ-መንግሥታዊ ተግባራትን አጠናቅራ፣ በእንግሊዘኛ እና በአማርኛ ቋንቋ የምትዘጋጅ ወርኃዊ መጽሔት ቀዳሚዋ ናት። መጽሔቷ፣ የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት በየዕለቱ የሚያወጣቸው መረጃዎች መሠረት በማድረግ ተጠንቅራ ትቀርባለች። መጽሔቷ የምትሸፍናቸው ርዕሰ-ጉዳዮችም፣ የምክር ቤቱን ዋና ዋና ሥራዎች የሆኑት ሕግ የማውጣት፣ አስርጂ መድረኮችን የማካሄድ፣ በዓመት ኹለት ጊዜ የሚደረጉትን የመራጭ ተመራጭ የውክልና ሥራዎችን፣ የአሥፈጻሚ ተቋማት ቁጥጥሮችን፣ የመስክ እና የተቋማት ጉብኙቶችን፣ የፓርላማ ዲፕሎማሲ እና የወዳጅነት ኮሚቴዎችን እና እንደራሴዎቹ ‘ራሳቸው ስለ ‘ራሳቸው የሚያከናውኗቸውን ተግባራት ታትታላች። ከእነዚኽ ጉዳዮች ባለፈም፣ በወሩ በእንደራሴዎቹ ከጸደቁ ሕግጋት አልያም ወሳኝ የምክር ቤቱ ተግባራት ላይ፣ የብሪጅን ኤዲቶሪያል ፖሊሲ ተንተርሳ ዳሰሳዊ ዕይታዎቿን ታቀርባለች።
- ብሪጅ፣ በየዓመቱ የእንደራሴዎቹን ምክር ቤት ጠቅላላ የሥራ ሁኔታ (ሕግ የማውጣት፣ አሥፈጻሚውን የመቆጣጠር፣ የውክልና ሥራ፣ የፓርላማ ዲፕሎማሲ እና ሌሎች ተጠቃሽ ሥራዎች) የሚያትት፣ “Parliamentary Audit/ Handbook of HoPR” የተሰኘ በተለያዩ ቋንቋዎች ተዘጋጅቶ የሚቀርብ ኃተታዊ ድርሳን ያስትማል። ይኽ በየዓመቱ የሚዘጋጅ ኃተታዊ ድርሳን፣ አራቱን ዋና ዋና የእንደራሴዎቹን ምክር ቤት፣ የቋሚ ኮሚቴዎችን እና የምክር ቤቱን ጽሕፈት ቤት ሥራዎች ብሎም ሌሎች ተያያዥ ክንውኖችን ዓለም ዓቀፋዊ በሆኑ የሕዝብ ተወካዮች ተቋማት መመዘኛዎች አንጻር በመገምገም የምክር ቤቱን ሥራ የሚያጎላ፣ የእንደራሴዎቹን አቅም የሚገነባ እና በአጠቃላይም የምክር ቤቱን ሥራ የሚደግፍ እና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታን የሚያጠናክር በአይነቱ በአገራችን የመጀመሪያ የሆነ እና ከኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና ከምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት ጋር ትብብር የሚዘጋጅ ነው፡፡
- “Parliament and Public Policy” የተሰኘ በእንግሊዘኛ ቋንቋ በየሦስት ወሩ የሚወጣ፣ በቀጠናው የሚገኙ አገራት የሕዝብ ተወካይ ምክር ቤቶች ላይ አትኩሮቱን ያደረገ ጥናታዊ መጽሔትም፣ የብሪጅ አንዱ አኹናዊ ተግባር ነው። የመጽሔቱ ዋና ዓላማ፣ የምሥራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግሥታት ድርጅት (ኢጋድ) አባል አገራት ማለትም የኢትዮጵያ፣ ጅቡቲ፣ ኤርትራ፣ ኬንያ፣ ሶማሊያ፣ ደቡብ ሱዳን፣ ሱዳን እና የኡጋንዳ በተጨማሪም የሶማሌ ላንድ የሕዝብ ተወካይ ምክር ቤቶችን በሚመለከት ጥናት እና ምርምርን ማጎልበት ነው። ይኽ መጽሔት የምክር ቤቶችን ሚና፣ አሠራር፣ ሕግ የማውጣት ሂደቶች፣ የቁጥጥር ሥልጣን እንዲሁም ከሕዝብ እና ከመንግሥት ጋር ያላቸውን ግንኙነት በጥልቀት የሚመረምሩ ጥናታዊ ጽሑፎችን የሚታተሙበት ነው። ዓላማውም፣ በቀጠናው በሚገኙ ዜጎች፣ በምሁራን፣ በፖሊሲ አውጪዎች እና በሌሎች ባለድርሻ አካላት መካከል በሕዝብ ተወካይ ምክር ቤቶች ጉዳዮች ላይ የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖር ማስቻል እና በምክር ቤቶች ሥራዎች ላይ የተመሠረተ ውይይት እና የፖሊሲ ማሻሻያዎችን ማበረታታት ነው። በመሆኑም፣ መጽሔቱ በቀጠናው የዲሞክራሲ ተቋማት ግንባታ እና ተግባራት ላይ ግንዛቤን በማስፋት በ‘የአገራቱ ለሚገኙ ምክር ቤቶች ተጠያቂነት እና ግልጽነት አስተዋጽኦ ያደርጋል። ከዚኹ ጋር በተያያዘም ብሪጅ፣ ከኢጋድ እና የየኢጋድ አባል አገራት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤቶች የጋራ ህብረት (Inter-Parliamentary Union of IGAD Member States) ጋር በትብብር ይሰራል፤ ሥራዎቹንም ያግዛል፡፡

## የትብብር ሥራዎች

- ብሪጅ ሪሰርች ኤንድ ኢኖቬሽን፣ ከ‘The Ethiopian House of Peoples' Representatives: Institutional Overview in the Post-2018 Reform Era After the 2018 Reform” የተሰኘ፣ የኢፌዲሪ የእንደራሴዎች ምክር ቤት ከ2010 ዓ.ም. የፖለቲካ ማሻሻያ አንስቶ ያሳየውን ተቋማዊ ለውጥ በስፋት የሚተነትን ጥናት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

ብሪጅ ሪሰርች ኤንድ ኢኖቬሽን፣ በአገራችን ጠንካራ ፌደራላዊ መንግሥት እና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲገነባ በሚመኙ እና በሚጥሩ ጥቂት ኢትዮጵያውያን ምሁራን የተመሠረተ ሀገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ሲሆን፣ የተመሠረተበትን አላማ ለማሳካትም በዋናነት ከኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና ከምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት ጋር በቅርበት እና በመናበብ መሥራት እንደሚያስፈልግ በጥብቅ ያምናል፡፡ በመሆኑም ብሪጅ እንደራሴን ጨምሮ በሥራዎቹ የምክር ቤቱን ተግባራት በቅንነት፣ የምክር ቤቱን ክብርና ሞገስ በጠበቀ እና በሀቀኝነት እና በሚዛናዊነት በመዘገብ ለሕዝብ መረጃ የሚያደርስ እና ከላይ ከተጠቀሱት ዋንኛ ሥራዎች እና ታላሚ ግቦች በተጨማሪ ከምክር ቤቱ ጋር በመመካከር የተለያዩ የአቅም ግንባታ፣ የጥናት እና ምርምር እና ሌሎች ተጓዳኝ የዲሞክራሲ ተቋማቶቻችንን ማጠናከሪያ ሥራዎችን አሀዱ ብሏል።

## የትብብር ሥራዎች

ብሪጅ ሪሰርች ኤንድ ኢኖቬሽን፣ ከ‘The Netherlands Institute for Multiparty Democracy (NIMD)’ ጋር በመሆን፣ “Ethiopian Parliament፦ After the 2018 Reform” የተሰኘ፣ የኢፌዲሪ የእንደራሴዎች ምክር ቤት ከ2010 ዓ.ም. የፖለቲካ ማሻሻያ አንስቶ ያሳየውን ተቋማዊ ለውጥ በስፋት የሚተነትን ጥናት በማድረግ ላይ ይገኛል።

- ብሪጅ ሪሰርች ኤንድ ኢኖቬሽን፣ በአገራችን ጠንካራ ፌደራላዊ መንግሥት እና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲገነባ በሚመኙ እና በሚጥሩ ጥቂት ኢትዮጵያውያን ምሁራን የተመሠረተ ሀገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ሲሆን፣ የተመሠረተበትን አላማ ለማሳካትም በዋናነት ከኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና ከምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት ጋር በቅርበት እና በመናበብ መሥራት እንደሚያስፈልግ በጥብቅ ያምናል። በመሆኑም ብሪጅ እንደራሴን ጨምሮ በሥራዎቹ የምክር ቤቱን ተግባራት በቅንነት፣ የምክር ቤቱን ክብርና ሞገስ በጠበቀ እና በሀቀኝነት እና በሚዛናዊነት በመዘገብ ለሕዝብ መረጃ የሚያደርስ እና ከላይ ከተጠቀሱት ዋንኛ ሥራዎች እና ታላሚ ግቦች በተጨማሪ ከምክር ቤቱ ጋር በመመካከር የተለያዩ የአቅም ግንባታ፣ የጥናት እና ምርምር እና ሌሎች ተጓዳኝ የዲሞክራሲ ተቋማቶቻችንን ማጠናከሪያ ሥራዎችን አሀዱ ብሏል።

እንደራሴ

እንደራሴ በብሪጅ ሪሰርች እና ኢኖቬሽን በየወሩ እየተዘጋጀ ይቀርባል፡፡

**ከራስ ውርድ፦**

“በእነዚኽ ወርኃዊ የእንደራሴዎቹ ጥቅንሮች ውስጥ ያሉት ኹሉም የገጸ-ሰብ እና የገጸ-መስኮች ምስሎች የተገኙት ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት ይፋዊ የመረጃ ምንጮች ነው፤ እንዲኹም፣ ኹሉም ቁጥራዊ ዘገባዎች የተወሰዱትም ከዚኽ ምንጭ ነው። ዳሰሳዊ ምልከታዎቹ፣ አጠቃሎዎች እና ተያያዥ ትንታኔዎቹ የተቋማችን ናቸው።”

# እንደራሴ

እንደራሴ በብሪጅ ሪሰርች እና ኢኖቬሽን በየወሩ እየተዘጋጀ ይቀርባል።

**BRIDGE** Research & Innovation for Democratic Governance and Enhanced Peace

+251 115 57 74 96

+251 911 86 12 34

research@bridge-et.org

https://bridge-et.org/

150096, Addis Ababa, Ethiopia.

Kazanchis, across the main gate of UNECA, SA Building, 9th Floor, Office No. 5, Addis Ababa.